# ብሔራዊ ስሜትን የለኮሰው ዶ/ር አብይ

Wednesday, 04 April 2018 14:20



ዶ/ር አቢይ አህመድ በገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ አቅራቢነት ከትላንት በስቲያ ሰኞ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሹመታቸው ከጸደቀ በኋላ ቃለመሀላ ፈጽመዋል፡፡ በዚሁ ዕለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጉት ንግግር ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ለአንባቢዎቻችን በተመቸ መልኩ ለማቅረብ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ጭብጦችን ንዑስ ርዕስ በመስጠት እንደሚከተለው አሰናድተነዋል፡፡

*** *** ***

*ሀገራችን ኢትዮጵያ በመንግስት አስተዳደር ስርዓቷ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በምታከናውንበት በዚህ ታሪካዊ ቀን በተከበረው ምክር ቤት ፊት ቀርቤ ይህን ንግግር ለማድረግ ስለበቃሁ የተሰማኝን ልዩ ክብር ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡ ከሁሉ አስቀድሜ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአገራችን ለተከሰተው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት የመፍትሄ አካል ለመሆን፣ የሀገር ክብርና ብሔራዊ ጥቅም በተሻለ ሁኔታ በአዲስ አመራር ሊጠበቅ ይችላል ብለው በማሰብ፣ ለአህጉራችን ምሳሌ በሆነ መልኩ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ላሸጋገሩት ለክቡር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ከፍ ያለ አክብሮቴን እገልጻለሁ፡፡ በተመሳሳይ የመንግስታዊ ስልጣን ሽግግሩ ያለ እንከን እንዲከናወን ልዩ ሚና ሲጫወቱ ለቆዩት ሁሉ በመላው ህዝባችን ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡*

## *ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት እና ለህዝብ መገዛት*

*በታሪካችን በተለያዩ አጋጣሚዎች አዲስ የፖለቲካ ምዕራፍ የመጀመር ዕድሎችን አግኝተን ብዙዎቹን በወጉ ሳንጠቀምባቸው አምልጠውናል፡፡ አሁንም፣ ይህ የስልጣን ሽግግር አዲስ ምዕራፍ የምንጀምርበት ሌላ ታሪካዊ ዕድል ነው፤ በመሆኑም በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት ልንጠቀምበት ይገባል፡፡*

*ኢትዮጵያ ማህፀነ ለምለም ናት፡፡ ከፍ ባለ የአገር ፍቅር መንፈስ ሰርክ የሚተጉ ልጆን አፍርታለች፡፡ ልጆቿም ወደቀድሞ ክብሯ እንድትመለስ፣ የሕዝቧ ሰላምና ፍትህ እንዲጠበቅ፣ ብልፅግና ያለ አድልኦ ለመላው ዜጎች ይዳረስ ዘንድ አጥብቀው ይመኛሉ… ይደክማሉ፡፡ በሀገር ውስጥና በውጪ ሆነው ስለ ሀገር አንድነትና ሰላም… ስለፍትህና እኩልነት… እንዲሁም ስለብልፅግና ይጮሃሉ.. ይሞግታሉ.. ይሟገታሉ፡፡*

*ይህ የሥልጣኔ ሽግግር ሁለት አበይት እውነታዎችን የሚያመለክት ነው፡፡ ክስተቱ፣ በአንድ በኩል በሀገራችን ዘላቂ፣ የተረጋጋና*

ሁሉን አቀፍ የህገ መንግስታዊ ስርዓት መሰረት ስለመጣላችን ማሳያ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከጊዜው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር እኩል የሚጓዝና በህዝብ ፍላጎት የሚገዛ፣ ህዝብን አለቃው አድርጎ የሚያገለግል ስርዓት እየገነባን መሆኑን ያመለክታል፡፡

## በተስፋና በስጋት መካከል ውስጥ ነን

መሪ ድርጅታችን ኢህአዴግ ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መስመሩን አጥብቆ በመያዝ ሀገራችንን ከሁለት አስርተ ዓመታት በላይ ባስተዳደረበት ወቅት በሁሉም መስክ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣ ህገ-መንግስታዊና ፌዴራላዊ ስርዓት ገንብቷል፡፡ ዓለም በአንድ አኩል በጥሞና፣ በአግራሞና በጉጉት በሌላ በኩል ደግሞ በስጋት እየተመለከተው ያለ ሀገራዊ ለውጥ ላይ እንገኛለን፡፡ ያሳካናቸው በርካታ ድሎች እንዳሉ ሁሉ በፍጥነት መቀረፍ የሚገባቸው በርካታ ጉድለቶች እንዳሉም እናምናለን፡፡ ከስህተቶቻችን ተምረን ወደ ፊት በመራመድ ማተኮር ያለብን ጉዳይ የተሻለች ሀገር ለሁላችንም በመገንባቱ ላይ ነው፡፡ ዋናው ቁም ነገር፣ አገራችንን ከፍ ወዳለ ምዕራፍ ማሸጋገሩ እና አንድነቷን ጠብቃ የምትቆይበትን ሁኔታ በቀጣይነት እያረጋገጡ መሄዱ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነት ያስተማረን እውነታ በጊዜያዊ ችግሮች ተሸንፎ መውደቅን ሳይሆን ፈተናዎችን ወደ ዕድልና መልካም አጋጣሚ ቀይሮ ድል መቀዳጀትን ነው፡፡

ትላንት፣ አባቶቻችን በመተማ፣ በአድዋ፣ በማይጨውና በካራ ማራ አጥንታቸውን ከስክሰው የከበረ ደማቸውን አፍስሰው በክብርና በአንድነት ያቆይዋት አገር አለችን፡፡ እኛ እድለኞች ነን፡፡ ውብ አገር- አኩሪ ታሪክ አለን፡፡ እኛ መነሻችንን እናውቃለን፡፡ በርካታ ዘመናትን የሚሻገር ታሪክ ያለው ታላቅ ህዝብ ነን፡፡ ህብረታችን ለአለም ምሳሌ መሆን ይችላል፡፡ ጠላቶቻችንን አንበርክኳል፡፡ ሉአላዊነታችንን ጠብቆ ዛሬ ላይ ከማድረሱም በላይ ለሌሎች ህዝቦችም የነፃነት ትግል አርአያ ሆኗል፡፡

## ማንነታችን እንዳይለያይ ሆኖ የተሰናሰለ፣ እንዳይነጣጠል ሆኖ የተገመደ፣ የተዋደደ እና የተዋሃደ ነው

አማራው በካራ -ማራ ለሀገሩ ለአላዊነት ተሰውቶ የካራ-ማራ አፈር ሆኖ ቀርቷል፡፡ ትግራይ በመተማ ከሀገሬ በፊት አንገቴን ውሰዱ ብሎ የመተማ አፈር ሆኗል፡፡ ኦሮሞው በአድዋ ተራሮች ላይ ስለሀገሩ ደረቱን ሰጥቶ የሀገሩን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ከአድዋ አፈር ተቀላቅሏል፡፡ ሱማሌው፣ ሲዳማው፣ ቤንሻንጉሉ፣ ወላይታው፣ ጋምቤላው፣ ጉራጌው፣ አፋሩ፣ ስልጤው፣ ከምባታው፣ ሐዲያው እና ሌሎቹም የኢትዮጵያ ህዝቦች ሁሉ በባድመ ከሀገሬ በፊት እኔን ብለው እንደወደቁ ከባድመ አፈር ጋር ተዋህደዋል፡፡ አንድ ኢትዮጵያዊ አባት እንዳሉት እኛ ስንኖር ሰዎች፣ ስናልፍ አፈር፣ ስናልፍ ሀገር እንሆናለን፡፡ የየትኛውንም ኢትዮጵያዊ ከቡር ስጋና ደም በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ አፈር ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡ ኢትዮጵያውያን ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያ እንሆናለን፡፡

## ኢትዮጵያ ከፖለቲካ አመለካከት በላይ ነች

በአንድ አገር ውስጥ የሀሳብ ልዩነቶች ይኖራሉ፡፡ የሀሳብ ልዩነት እርግማን አይደለም፡፡ ልዩነቱ እንዳለ ሆኖ መደማመጥና በመርህ ላይ ተመስርተን መግባባት ስንችል የሀሳብ ልዩነት በረከት ይዞልን ይመጣል፡፡ በሀሳብ ፍጭት ውስጥ መፍትሄ ይገኛል፡፡ በመተባበር ውስጥ ኃይል አለ፡፡ ስንደመር እንጠነክራለን፡፡ አንድነት የማይፈታው ችግር አይኖም... አገር ይገነባል፡፡ የኔ ሀሳብ ካላሸነፈ ሞቼ እገኛለሁ ማለት ግን እንኳን አገርን ሊያቆም ቤተሰብን ያፈርሳል፡፡ ያለችን አንድ ኢትዮጵያ ነች ከየትኛውም የፖለቲካ አመለካከት በላይ አገራዊ አንድነት ይበልጣል፡፡ አንድነት ማለት ግን አንድ አይነትነት ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

አንድነታችን ልዩነቶቻችንን ያቀፈ ብዝሃነታችንን በህብረ-ብሔራዊነት ያደመቀ መሆን አለበት፡፡

## ነፃነት ከመንግስት ለህዝብ የሚበረከት ስጦታ አይደለም

ዲሞክራሲ ለኛ ባዕድ ሃሳብ አይደለም፡፡ በዓለም ውስጥ በብዙ ማህበረሰቦችና ሃገራት ዲሞክራሲ በማይታወቅበት ዘመን በገዳ ሥርዓታችን ተዳድረን ለዓለም ተምሳሌት ሆነን፣ ኖረናል፡፡ አሁንም ዲሞክራሲን ማስፈን ከየትኛውም ሀገር በላይ ለኛ የህልውና ጉዳይ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ዲሞክራሲ ያለነፃነት አይታሰብም፡፡ ነፃነት ከመንግስት ለሕዝብ የሚበረከት ስጦታም አይደለም፡፡ ከሰብዓዊ ክብር የሚመነጭ የእያንዳንዱ ሰው የተፈጥሮ ፀጋ እንጂ፡፡ ነጻነትን በዚህ መልኩ ተረድቶ እውቅና የሰጠውን ሕገ መንግሥታችንን በአግባቡ መተግበር፣ የሰባዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተለይም ሃሳብን የመግለፅ፣ የመሰባሰብና የመደራጀት መብቶች በህገ መንግስታችን መሠረት ሊከበሩ ይገባል፡፡ የዜጎች በሀገራችን የአስተዳደር መዋቅር በዲሞክራሲያዊ አግባብ በየደረጃው የመሳተፍ መብትም ሙሉ በሙሉ እውን መሆን አለበት፡፡

ሁላችንም መገንዘብ ያለብን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ መደማመጥን ይጠይቃል፡፡ ሕዝብ አገልጋዩን የመተቸት፣ የመምረጥ፣ የመጠየቅ ሙሉ መብት አለ፡፡ መንግሥት የህዝብ አገልጋይ ነው፡፡ ምክንያቱም ገዢ መርሃችን የህዝብ ሉዓላዊነት ነውና፡፡ በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ውስጥ፣ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም መርህ፣ በመደማመጥ የሀሳብ ልዩነትን ማስተናገድ መሆን አለበት፡፡ ኢትዮጵያ የጋራችን፣ የኛ የሁላችን መሆኗን ተገንዝበን የሁሉም ድምፅ የሚሰማበት፣ ሁላችንንም የሚያሳትፍ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የመገንባቱን ትግል አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡

ዲሞክራሲ ሲገነባ መንግስት የዜጎችን ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ማክበር አለበት፡፡ ዲሞክራሲን ከዜጎች ሰላማዊ እንቅስቃሴና ከመንግስት መሪነት፣ ደጋፊነትና ሆደ ሰፊነት ውጭ ማዳበር አይቻልም፡፡ በመሆኑም መንግስት የዜጎች ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንዳይስተጓጎል በፅናት ይሰራል፡፡

በተመሳሳይ ዜጎች ሀሳባቸውን ሲገልፁ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መሆን ይገባዋል፡፡ የራስን ዲሞክራሲያዊ መብት እየጠየቁ የሌላውን መብት መጋፋት እርስ በእርሱ ይጣረሳል፣ ዲሞክራሲንም ያቀጭጫል፡፡ መንግስት ህግን ማክበር አለበት፣ ማስከበርም ግዴታው ነው፣ ታጋሽነትም ኃላፊነቱ ነው፡፡ የመንግስት ታጋሽነት ሲጓደልም ዲሞክራሲ ይጎዳል፡፡ በሁለቱም አካሄድ የምንናፍቀው ዲሞክራሲ ሊመጣ አይችልም፡፡

በዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ውስጥ የህግ የበላይነት መስፈን ይገባዋል፡፡ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን በምናደርገው ትግል መርሳት የሌለብን ቁም ነገር ህዝባችን የሚፈልገው የሕግ መኖርን ብቻ ሳይሆን የፍትህ መረጋገጥንም ጭምር ነው፡፡ የህዝብ ፍላጎት ከፍትህ የተፋታ ደረቅ ሕግ ሳይሆን፣ በፍትህ የተቃኘ፣ ለፍትህ የቆመ የሕግ ስርዓትን ነው፡፡ የህዝብ ፍላጎት የሕግ አስከባሪ ተቋማት ገለልተኛና ለፍትህ ታማኝ፣ ለዜጎች መብት ቀናኢ እንዲሆኑ ነው፡፡ ህግ ሁላችንንም እኩል የሚዳኝ መሆን አለበት፡፡ እንዲህ ሲሆን ህግ በተፈጥሮ ያለንን ሰብዓዊ ክብራችንን ያስጠብቅልናል፡፡ ይህን እውነታ በመረዳት በሀገራችን ዲሞክራሲ እንዲያብብ፣ ነፃነትና ፍትህ እንዲሰፍን፣ የህግ የበላይነት እውን እንዲሆን አስፈላጊውን ማሻሻያ በማድረግ በዘርፉ ያለውን ክፍተት እንሞላለን፡፡

ለሰላም መሠረቱ ፍትህ ነው፡፡ ሰላም የግጭት አለመኖር ብቻ አይደለም፡፡ ሰላም በመግባባት ላይ የተመሰረተ ፅኑ አንድነታችን ነው፣ ሰላም መተማመናችን ነው፡፡ ሰላም - በሁላችንም ፈቃድ ዛሬም የቀጠለ የአብሮነት ጉዞአችን ነው፡፡ ሰላም አለመግባባትና ተቃርኖዎችን በሰለጠነ መንገድ መፍታት የሚያስችለን መንገድና ግባችን ነው፡፡

## ለኤርትራ መንግሥት የቀረበ የሰላም ጥሪ

ያለንበት ጊዜ የአፍሪካ ቀንድ በቀውስ ውስጥ ያለበት፣ ብዙ የየራሳቸው ፍላጎና ዓላማ ያላቸው ኃይሎች የሚራኮቱበት፣ ውስብስብ መጠላለፍ በቀጠናው ያለበት ወቅት ነው፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ በደም፣ በባህል፣ በቋንቋ እና በረጅም ጊዜ የጋራ ታሪክ የተሳሰርን ህዝቦች ያለንበት አካባቢ ነው፡፡ የውጭ ግንኙነታችንን በተመለከተ ሀገራችን የፓን አፍሪካኒዝም መሰረት፣ የአፍሪካ ህብረት መስራችና መቀመጫ፣ የቀደምት ዓለም አቀፍ ተቋማት መስራችና በዓለም አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ እንዲሁም ቀጠናው ጉዳዮች ላይ ጉልህና ገንቢ ሚና የምትጫወት ሀገር ናት፡፡ ይህንኑ በጋራ ተጠቃሚነትና እኩልነት ላይ የተመሰረተውን ፖሊሲያችንን አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡ ከአፍሪካዊያን ወንድሞቻችን ጋር በአጠቃላይ፣ እና ከጎረቤቶቻችን ጋር በተለይ በችግርም በተድላም አብረን እንቆማለን፡፡ ከኤርትራ መንግስት ጋር ለዓመታት ሰፍኖ የቆየው አለመግባባት እንዲያበቃም ከልብ እንፈልጋለን፡፡ የበኩላችንንም እንወጣለን፡፡ በጥቅም ብቻ ሳይሆን በደም ለተሳሰሩት የሁለቱ ሀገር ህዝቦች የጋራ ጥቅም ሲባል

ልዩነቶቻችንን በውይይት ለመፍታት ያለንን ዝግጁነት እየገለፅኩ የኤርትራ መንግስትም ተመሳሳይ አቋም እንዲወስድ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

## አንዱ ሰርቶ ሌላው ቀምቶ የሚኖርባት ሀገር አትሆንም

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የህዝባችንን ብሶት ካጋጋሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ ሙስና አንዱ ነው፡፡ ሙስናን ጸረ-ሙስና ተቋም በመመሥረት ብቻ መከላከል እንደማይቻል ተረድተን፣ ሁላችንም፣ ኢትዮጵያችን፣ አንዱ ሰርቶ ሌላው ቀምቶ የሚኖርበት አገር እንዳትሆን ለመጠበቅ የምንችለውን ሁሉ እንድናደርግ በትህትና እጠይቃችኋለሁ፡፡

ትናንት የተፈጠረን ሃብት ከሌላው በመቀማት ሂሳብ ለማወራረድ የሚተጋ አገርና ሕዝብ ወደፊት ለመራመድ አይችልም፡፡ ገበታው ሰፊ በሆነባት፣ ሁሉም ሰርቶ መበልፀግ በሚችልባት ኢትዮጵያችን አንዱ የሌላውን ለመንጠቅ የሚያስገድድ ይቅርና የሚያሳስብ ምንም ምክንያት የለም፡፡ ይልቁንም ወቅቱ የፈጠረልንን ልዩ አጋጣሚና ሃገራዊ አቅማችንን አቀናጅተን የእጥረትና እጦት አስተሳሰብን በማስቀረት ለጋራ ብልፅግና እንትጋ፡፡ ታዋቂው የህንድ የነፃነት ንቅናቄ መሪ ማህተመ ጋንዲ በአንድ ወቅት እንደተናገረው፣ አገር ለሁሉም የሚሆን በቂ ሀብት አላት፣ ሁሉም እንደልቡ የሚዘርፈው ሀብት ግን ሊኖራት አይችልም፡፡ አሁን በጀመርነው አዲስ ምዕራፍ፣ ዘረፋን፣ የሀብት ብክነትን እና የተደራጀ ሙስናን፣ መላው ህዝባችንን በሚያሳትፍ እርምጃ ለመመከት ሌት ተቀን እንተጋለን፡፡

## ግብርናው በቴክኖሎጂ አልታገዘም

ሀገራችን ባለፉት ዓመታት ባስመዘገበችው ፈጣን እድገት የተነሳ በድህነት ቅነሳ፣ በመሠረተ ልማት ግንባታ፣ በሰው ኃይል ልማት እና በመሳሰሉት ያገኘናቸው ስኬቶች ለሁሉም የሚታዩ ናቸው፡፡

ከዚህ አኳያ መንግስት የዋጋ ንረት እና የውጪ ምንዛሪ ዋጋን ለማረጋጋት፣ የፋይናንስ ዘርፉን ጤናማነት ለመጠበቅ፣ ለኢኮኖሚ የሚቀርበውን የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት እና አካታችነትን ለማስፋት፣ የውጪ ምንዛሪ ግኝትን እንዲሁም ቁጠባን እና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ የስራ እድል ለመፍጠር፣ የህዝቡን የነፍስ ወከፍ ገቢ ለማሳደግ እንዲሁም አስከፊ ድህነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ የፖሊሲ እና የትግበራ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡



በአንጻሩ፣ ባለፉት ዓመታት በተለያዩ ጊዜያት የኢኮኖሚ እድገቱና እና የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋቱን የሚፈታተኑ ተግዳሮቶች ተከስተዋል፡፡ ከእነዚህም ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የውጪ ንግድ በምንፈልገው መጠን አለማደጉ፣ ይሄን ተከትሎ የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት እና ፍላጎት አለመመጣጠን፣ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት፣ የውጪ እዳ ጫና እና የሀገር ውስጥ ቁጠባና ኢንቨስትመንት መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መምጣቱ ናቸው፡፡ በግብርናው ዘርፍ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች አበረታች ቢሆኑም ዘርፉን በተገቢው ሁነታ በቴክኖሎጂ መደገፍ ባለመቻሉ እንደ ሀገር ማግኘት የሚገባንን የኢኮኖሚ ትሩፋት ሳናገኝ ቆይተናል፡፡ እንደ ትልቅ ሀገር እና ህዝብ ከምናስበው የስኬት ጫፍ ላይ መድረስ የምንችለውና ችግሮቻችንን የምንፈታበትን ዋና ቁልፍ የምናገኘው በትምህርት እና በትምህርት ብቻ እንደሆነ በማመን መንግስት ለትምህርት ዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ቢሆንም በተለይ የትምህርትን ጥራት ከማስጠበቅ አንጻር እጅግ ብዙ የቤት ስራዎች ከፊታችን እንዳሉ በውል በመገንዘብ በርካታ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ የትምህርት መስፋፋት ይበል የሚያሰኝ የመንግስታችን ስኬት ቢሆንም ይህ የትምህርት ሽፋን እድገት በጥራት እስካልተደገፈ ድረስ ልፋት ጥረታችን ሁሉ የምንተጋለትን ውጤት ሊያመጣልን አይችልም፡፡ በመሆኑም ከመጀመርያ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉትን የእውቀት አለሞቻችንን በጥራት ላይ አተኩረው እንዲሰሩ መንግስት በፍፁም ቁርጠኝነት ይረባረባል፡፡ በተለይም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን እና ከቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች የሚወጡት ተማሪዎቻችን

ከሚገበዩት እውቀት የሚነፃር ክህሎት እንዲኖቸው ከፍተኛ ጥራት ይደረጋል፡፡

እነዚህንና ሌሎቹንም ችግሮቻችንን ለመቅረፍ የሁለተኛውን የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን የሁለት ዓመት ተኩል አፈጻጸም በመገምገም አስፈላጊ የሆኑ የፖሊሲ እርምጃዎችን በመውሰድ፣ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትን ለማስቀጠል እንተጋለን፡፡

## የወጣቱ ጥያቄ ከኢኮኖሚ በላይ ነው

ኢትዮጵያ የናንተ ነች፣ መጭውም ዘመን ከሁሉ በላይ የእናንተ ነው፡፡ አሁንም የአገሪቷን በመገንባት ግንባር ቀደም ሆናችሁ መሳተፍ ይኖርባችኋል፡፡ የወጣቱ ጥያቄ የኢኮኖሚና የእኩል ተጠቃሚነት ብቻ ሳይሆን የዴሞክራሲና የፍትህ ነው ብለን እናምናለን፡፡ የሁሉም ዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት፣ ማህበራዊ ፍትህ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ከማሳደግ አንጻር ክፍቶች ነበሩ፡፡

አገራችን፣ ጥሩ የሚባል ኢኮኖሚያዊ እድገትን እያስመዘገበች እንደመሆነ ቢታወቅም እድገቱ በቅርጽና በይዘት ተለዋዋጭ የሆነውን የወጣቱን ትውልድ ፍላጎት በሚፈለገው ደረጃ የሚያረካ አልነበረም፡፡ ይህም፣ ሕዝባችንን ለብሶት እንደዳረገው እንገነዘባለን፡፡ ያለወጣቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት አገር የትም ልትደርስ እንደማትችልም እንረዳለን፡፡ ኢትዮጵያ ለወጣቶቿ ተስፋ የምትሰጥ እንጂ፣ ተስፋ የምታስቆርጥ አገር እንዳትሆን የምንችለውን ሁሉ እንደምናደርግ ቃል እገባለሁ፡፡ በሚቀጥሉት ጊዜያት ለወጣቱ የስራ እድል መፍጠር ብቻ ሳይሆን ወጣት ባለሀብቶች በብዛት እንዲፈጠሩ እንሰራለን፡፡ ለዚህ እንቅፋትና መሰናክል የሚሆኑ አመለካከቶችና የተንዛዙ አድሏዊ የሆኑ አሰራሮችን አስወግደን ፍትሃዊ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት እንዲኖረን መንግሥት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ መርሳት የሌለብን ሀቅ ግን ለራሱም ሆነ ለሀገሩ በሥራውና በጥረቱ ሀብት የሚፈጥረው ወጣቱ እራሱ መሆኑን ነው፡፡

## ሴቶችን የምናግዘው ለህልውናችን ነው

በብዙ አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ኢትዮጵያን ገንብታችሁ፣ ታሪክ ሰርታችሁ፣ ትውልድ ቀርፃችሁ ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ በትግላችሁም የተሻለች ሀገር እንድትኖረን ብዙ መስዋዕትነት ከፍላችኋል፡፡ ትግላችሁ የፍትህ ትግል ነው፣ ትግላችሁ ክቡር ትግል ነው፣ ትግላችሁ ትግላችን ነው፡፡ መንግስት የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና በሀገራችን ሁለንተናዊ የእድገት ግስጋሴ ውስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ለማስቻል የተለያ ስራዎችን በመስራት ላይ የሚገኝ ቢሆንም አሁንም ከሰራነው ይልቅ ያልሰራናቸው ስራዎች እጅግ እንደሚበዙ እናምናለን፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የሀገራችን ሴቶች ተፈጥሮ እና ኑሮ የሰጧችሁን በረከቶች ተጠቅማችሁ ለሀገራችን እድገት እና ብልፅግና እንዲሁም ለፖለቲካችንም ስምረት አዎንታዊ ሚና እንደምትጫወቱ ተስፋዬ የላቀ ነው፡፡

አገራዊ ማንነታችን ያለ እናንተ ያለ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ምንም ነው፡፡ አገሪቷን የገነቡ፣ ያገለገሉ፣ ያቆሙ ሴቶችና እውቅና በመንፈግ ሀገራዊ ትንሳኤን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ መንግስታችን ለሴቶች መብትና እኩልነት የሚቆመው፣ ለሴቶቻችን ውለታ ለመዋል ሳይሆን ለሁላችንም ብለን ነው፡፡ ግማሽ አካሉን የረሳ ሀገር ሙሉ የሀገር ስዕል ይኖረው ዘንድ ከቶ እንደማይችልና ወደፊትም እንደማይራመድ መንግስት በውል ይገነዘባል፡፡ በመሆኑም መንግስታችን ከዚህ ቀደም ከነበረው ፍጥነት እና የትግበራ ስኬት በላቀ መልኩ ለሴቶች ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት በቁርጠኝነት ይሰራል፡፡

## በአንድ ጀንበር የሚፈታ ችግር የለም

የዳበረ የዲሞክራሲ ባህል አለመኖር፣ ሥር የሰደደ ድህነት፣ የተደራጀ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መስፋፋት፣ የመልካም አስተዳደር እጦት ተደማምረው ሰፊና ውስብስብ ፈተና ደቅነውብናል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በርካታ ወገኖቻችን ከመኖርያ ቀዬአቸው ለመፈናቀል፣ ለህይወት እና ለንብረት መጥፋት ተዳርገው እንደነበር ይታወሳል፡፡ ዜጎች በሀገራቸው ውስጥ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር እና ሃብት የማፍራት መብታቸው መከበር አለበት፡፡ በመሆኑም እንደዚህ አይነት ተገቢ ያልሆነ ድርጊት እንዲያበቃና ዳግም እንዳይፈጠር መሥራት ይኖርብናል፡፡

ችግሮቻችንን፣ ተለያይተን ቀርቶ ተባብረን እና ተዋደንም ለመፍታት ዓመታት ያስፈልጉናል፡፡ በመሆኑም የባከነውን ግዜ በማካካስ ወደፊት መጓዝ እንችል ዘንድ በአዲስ መንፈስ መረባረብ ይጠበቅብናል፡፡

ሁሉም ችግሮቻችን በአንዲት ጀንበር ሊፈቱ አይችሉም፡፡ ነገር ግን የጀመርነውን የተሻለች ሀገር የመገንባት ሂደት ማፋጠን እንችላለን፡፡ የተሻለች አገር መገንባት የሚያስችል ጠንካራ ተነሳሽነት አለ፡፡ ጠንካራ አገር ለመገንባት ሁላችንም ኃላፊነት አለብን፡፡ እንደ ተለያየ አገር ዜጋ በባእድነት እና ባይተዋርነት ሳይሆን፣ ሁላችንም እንደ ባለቤቶች እጅ ለእጅ ተያይዘን መጓዝ ይጠበቅብናል፡፡ ይህ ሲሆን ስንወድቅም፣ ስንነሳም በጋራ ይሆናል፡፡

በቀሪው የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዓመታት ቀሪ የልማት መርሀ-ግብሮቻችንን በፈጠነ ጊዜ ለማሳካት ጥረት ይደረጋል፡፡ ከመደበኛው የሥራ ሰዓታችን በሚሻገር ጊዜ፣ ከፍ ባለ ፍጥነትና ተነሳሽነት በመሥራት በቅርብ ዓመታት ውስጥ በተከሰተው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት የደረሰብንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳት ለማካካስ አገራዊ ንቅናቄ እንድናደርግ ከአደራ ጭምር መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡

## በውጭ ሀገራት ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የቀረበ ጥሪ

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለስራም ሆነ ለትምህርት በሄደበት ሁሉ ኢትዮጵያን ተሸክሟት ይዞራል፡፡ ኢትዮጵያዊውን ከኢትዮጵያ ታወጡት እንደሆነ ነው እንጂ ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያዊው ልብ ውስጥ አታውጧትም የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ ሁላችሁም በታታሪነታችሁ፣ በልቀታችሁ እና የትም በሚከተላችሁ የሀገራችሁ የጨዋነት ባህሪ የኢትዮጵያና የእሴቶቿ እንደራሴዎች ናችሁ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ከኢትዮጵያ ያነሰ የተፈጥሮም ሆነ የታሪክ ሀብት ባላቸው ነገር ግን እጅግ በበለፀጉ ሀገራት ውስጥ ራሳችሁን ስታገኙት ስለሀገራችሁ ቁጭት ሳይሰማቹ አይቀርም፡፡ ሁላችንም ውስጥ ያ ቁጭት አለ፡፡ እንደሀገር ያለንን ሃብት አሟጠን ለመጠቀም የምናደርገው ጥረት በቂ ሳይሆን ሲቀር መቆጨታችሁ አይቀርም፡፡ መቆጨትም አለባችሁ፡፡ ይሄንንም ሁኔታ ለመለወጥ ለሁላችንም የምትበቃ በዚያው ልክ ግን የሁላችንንም ተሳትፎ የምትፈልግ ሀገር አለችንና እውቀታችሁንና ልምዳችሁን ይዛችሁ ወደሀገራችሁ መመለስና ሀገራችሁን አልምታችሁ መልማት ለምትሹ ሁሉ እጃችንን ዘርግተን እንቀበላችኋለን፡፡ በውጭ ሀገራት ኑሯችሁን ላደረጋችሁትም ቢሆን በማንኛውም መልኩ በሀገራችሁ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንድትሆኑና ሀገራችንን በሁሉም መልክ ለመቀየር ለምታደርጉት አስተዋጽኦ መንግስት ያልተቆጠበ ድጋፍ ማድረጉን ይቀጥላል፡፡

## እገዛችሁ አይቋረጥብን


ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ንግግር ሲያደርጉ

እስከዛሬ ባደረግነው የሰላምና የልማት እንቅስቃሴ ከጎናችን የቆማችሁ የልማት አጋሮቻችን የአገራችን ጥብቅ ወዳጆች እንደሆናችሁ እንገነዘባለን፡፡ የአገራችንን ልማት እና ሠላም ለማረጋገጥ በምናደርገው ጥረት እንደ ወትሮ ሁሉ ከጎናችን እንደምትቆሙ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ፡፡

## መጪው ጊዜ በኢትዮጵያችን የፍቅርና የይቅርታ ጊዜ ነው!

ሀገራችን ፍትህ፣ ነፃነትና ሰላም የሰፈኑባት፣ ዜጎቿ በሰብዓዊነት የሚተሳሰቡባት፣ በእህት/ ወንድማማችነት የተሳሰሩባት እንድትሆን እንፈልጋለን፡፡ ይህ ህልማችን ዕውን የሚሆነው ከእንቅልፋችን ነቅተን ስንሰራ ነው፡፡ መመኘታችን መልካም ነው፡፡ ነገር ግን ምኞታችን ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ መሥራት፣ መትጋት፣ መታገል ይጠበቅብናል፡፡ በመጀመሪያ ሥራችን ልናደርገው የሚገባንና ትግላችን ማተኮር ያለበት ራሳችን ላይ ነው፡፡ አመለካከታችንን ከጥላቻ፣ ከቂም በቀል ስሜትና ከዘረኝነት ማፅዳት ይገባናል፡፡ በብሔር፣ በፆታ በፖለቲካ አመለካከት፣ በሃይማኖት... ወዘተ ያሉንን ልዩነቶች እንደ በረከትነታቸው በፍቅር

በማስተናገድ ከልዩነቶቹ የሚነሳ አለመግባባት ቢኖር እንኳ ከፍትህ እንጂ ከበደል ጋር ባለመተባበር ሞራላዊ እይታዎቻችንን ልናስተካከል ይገባል፡፡ ፍትህ ዋናው መርሃችን፣ ለሰው ልጆች ሁሉ ፍቅርና ክብር የሞራል መልህቃችን ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ ሰርተን የማናገባድደው፣ ሁሌም ልፋት፣ ሁሌም ትግል የሚጠይቅ የእድሜ ዘመን ሁሉ የቤት ሥራ ነው፡፡

ሀገራችን በአሁኑ ወቅት ለደረሰችበት ምዕራፍ በርካታ ትውልዶች መስዋዕት ሆነዋል፡፡ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን እውን እንዲሆንም አእላፎች ተሰውተዋል፡፡ ታዳጊውን ዴሞክራሲያችንን ለማዳበር ግን ተጨማሪ የህይወትም ሆነ የአካል መስዋእትነት አያስፈልገንም፡፡ ባለፉት ዓመታት እንደመንግስትም እንደ ዜጎችም ከዴሞክራሲ ባህላችን አለመዳበር ጋር ተያይዞ በታዩብን እጥረቶች በዜጎቻችን ህይወት እና በግልም በጋራም ንብረቶቻችን ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት ደርሷል፡፡ ይህንን ሁላችንም ማስቀረት እንችልና ይገባንም ነበር፡፡ በተለያየ ጊዜ፣ መስዋዕትነት ለከፈሉ የሙብት ተከራካሪዎችና ፖለቲከኞች፤ በቅጡ ሳይቦርቁ ህይወታቸው ለተቀጠፈ ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች፣ ለስነልቦናዊና አካላዊ ቀውስ ለተዳረጉ ቤተሰቦችና ግለሰቦች ከልብ የመነጨ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ እንዲሁም ሰላም ለማስከበርና ህገመንግስታዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ሲንቀሳቀሱ ህይወታቸውን ላጡ የፀጥታ ኃይሎች አባላት ለከፈሉት መስዋእትነት ያለኝን አድናቆትና አክብሮት ለመግለፅ እፈልጋለሁ፡፡ ለተፈጠሩ ችግሮች እልባት በማበጀት ህዝባችንን እንደምንክስም ጭምር በዚሁ አጋጣሚ ቃል እገባለሁ፡፡

በአገር ውስጥም ሆነ በስደት ከአገር ውጭ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ በሙሉ ከልባችን ይቅር ተባብለን፣ የትናንትናውን ምዕራፍ ዘግተን፣ በብሔራዊ መግባባት ወደ ቀጣይ ብሩህ ሀገራዊ ምዕራፍ እንሻገር ዘንድ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

## ከተቃዋሚ ወደ ተፎካካሪ የፖለቲካ ትርክት

ከኢህአዴግ ውጪ ያሉ ፓርቲዎችን የምናይበት መነፅር እንደተቃዋሚ ሳይሆን እንደተፎካካሪ፣ እንደጠላት ሳይሆን እንደ ወንድም፣ አማራጭ ሃሳብ አለኝ ብሎ እንደመጣ አገሩን እንደሚወድ የዜጋ ስብስብ ነው፡፡ ስለዚህ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ የተመቻቸና ፍትሃዊ የመወዳደርያ ሜዳ እንዲኖር በመንግስት በኩል ፅኑ ፍላጎት ያለ በመሆኑ ስለሰላምና ፍትህ በልዩ ልዩ መንገድ የምትታገሉ የተፎካካሪ ፓርቲ መሪዎች፣ አብሮነታችንንና ሰላማችንን አደጋ ላይ የሚጥሉ፣ ብሄራዊ ጥቅሞቻችንንም አሳልፈው የሚሰጡ የአስተሳሰብ መስመሮችን በአርቆ አስተዋይነትና ሀገራዊ ፍቅር፣ በሰጥቶ መቀበል መርህ የተሻለ የፖለቲካ ባህል ለመፍጠር የምናደርገውን ጥረት እንድታግዙ ጥሪዬን አስተላልፋሁ፡፡

የሃገራችን አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች፣ በሁሉም ደረጃ የምትገኙ የሀገራችን የፀጥታ ኃይሎች፣ ምሁራን፣ ባለሀብቶች፣ በገጠርም ሆነም በከተማ የምትገኙ የተለያየ ሞያ ባለቤቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖ፣ ዋቄፈታዎች እንዲሁም ሌሎች ሃይማኖቶችን የምትከተሉ ወገኖች፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ የምትገኙ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ ሁላችንም የዳበረ ዴሞክራሲ ለመገንባት እንረባረብ! አገራችንን ከድህነት አዘቅት ውስጥ ለማውጣት እንትጋ! ዘረኝነትና መከፋፈልን ከአገራችን እናጥፋ! የተማረና በምክንያት የሚከራከር ዜጋ እንፍጠር!

የዛሬው እለት በአኩሪ ኢትዮጵያዊ ወኔ የተጀመረው ታላቁ የህዳሴ ግድባችን ሰባተኛ ዓመት ነው፡፡ በዚህ ግድብ ግንባታ የታየው አንድነት እና መሰባሰብ የሀገራችንን ችግሮች በሙሉ መቅረፍ እና መሻገር እንደምንችል ያረጋገጠልን በመሆኑ ይህንኑ መንፈስ ይዘን ከግድቡ መጠናቀቅ ባሻገር የሀገራችንን ብልጽግና እስከምናረጋግጥበት ከፍታ ድረስ እንድንዘልቅ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

## ምስጋናና ዕውቅና

በመጨረሻም በዚህ ወቅት ሀገሬን እና ህዝቤን ለማገልግል ይህንን ከባድ ኃላፊነት ስቀበል አመሰግናቸው ዘንድ የሚገቡኝን አካሎች እንዳመሰግን ትፈቅዱልኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

በመጀመሪያ ለዚህ ኃላፊነት የመረጡኝና እምነት የጣሉብኝ ድርጅቴ ኢህአዴግን እና የአገሬን ህዝብ በተለየ አክብሮት እና ፍቅር አመሰግናለሁ፡፡

ሁለተኛ የሰባት ዓመት ልጅ እያለሁ እንዲህ ከፊታችሁ እንደምቆም የምታውቅ እና ይህንን ሩቅ ጥልቅ እና ረቂቅ ራዕይ በውስጤ የተከለች፣ ያሳደገች እና ለፍሬ ያበቃች አንዲት ኢትዮጵያዊት እናት እንዳመሰግን በትህትና እጠይቃለሁ… ይህች ሴት እምዬ ናት፤

እናቴ ከሌሎቹ ቅን የዋህ እና ጎበዝ ኢትዮጵያውያን እንደ አንዶቹ የምትቆጠር ናትና ቁሳዊ ሃብት ብቻ ሳይሆን አለማዊ እውቀትም የላትም፡፡ በእናቴ ውስጥ ሁሉንም የኢትዮጵያ እናቶች ዋጋ እና ምስጋና እንደመስጠት በመቁጠር፣ ዛሬ በህይወት ካጠገቤ ባትኖርም ውዷ እናቴ ምስጋናዬ ከአፀደ ነፍስ ይደርሳት ዘንድ በብዙ ክብር ላመሰግናት እወዳለሁ፡፡ ሌሎች ኢትዮጵያውያን እናቶቼ በልጆቻቸው የነገ ራዕይ ላይ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው በመገንዘብ ነገ ለሚያጭዱት መልካም ፍሬ ዛሬ ላይ የሚዘሩት ዘር ዋና ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ለሚከፍሉት መስዋእትነት ያለኝን በምንም የማይተካ አድናቆት ምስጋና እና ክብር በብዙ ልባዊ ፍቅር ሳቀርብ በቀጣይም ልጆቻችን የዚህች ሀገር ህዳሴ እንዲረጋገጥ ዋና ተዋንያን መሆን እንዲችሉ እናታዊ አይተኬ ሚናችሁን እንድትወጡ አደራ በማለትም ጭምር ነው፡፡

ሶስተኛ የሚስቶች ስኬት ሁለት ሶስት ነው፡፡ ሁለት ሲሆን፤ አንዱ የራሳቸው ሌላው የባላቸው፡፡ ሶስት ሲሆን ደግሞ የልጆቻቸውም ይጨመርበታል፡፡ አንዳንዴ ድል ስኬታቸው ከዚህም ይሻገራል፡፡ የእናቴን ራዕይ ተረክባ በብዙው የደገፈችኝና የእናቴ ምትክ የሆነችልኝ ውዷ ባለቤቴ ወ/ሮ ዝናሽ ታያቸው ከነዚህ ሚስቶች ተርታ ትመደባለችና እጅግ አድርጌ ላመሰግናት እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም ከትግል ጓዶቼ እና በዝለት ጊዜ ብርታት፣ በድካም ጊዜ ሃይል ከሆኑኝ የቅርብ - የሩቅ ወዳጆቼ ውጪ ዛሬ እኔ ከፊታችሁ መቆም ባልቻልኩ ነበር፤ ለሁላችሁም ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

"ኢትዮጵያ በልጇ ጥረት ታፍራ፣ ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!"

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ!

አመሰግናለሁ!!!

ክጠቕላይ ሚኒስትሩ በዓለ-ሲመት ሥነ-ሥርዓት በከፊል

